# የኢሮብ ታሪክ ጥያቄዎችና አባባሎች

ከግርማይ ተስፋገርግስ

ክፍል ሁለት

በክፍል አንድ ከመቶ ዓመት በፊት የተፃፉት ሁለት አፈ-ታሪኮችን አይተን ነበር። ከሁለቱ ውስጥ አንደኛው የተፃፈው በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን የኢሮብ ህዝብ ቅድመ አያት ወረደ-ምሕረት ሆኖ፤ የአፄ ይትባረክ ልጅ እንደሆነ በመጥቀስ የኢሮብ ህዝብን ትውልድ ከላስታው ሥርወ-መንግሥት ጋር ያያይዟል። ሁለተኛው ደግሞ በትግርኛ ቋንቋ የተፃፈ ሲሆን የኢሮብ ህዝብን ትውልድ ከእሥራኤልና ከሮማ ነገሥታት ጋር በማያያዝ ቅድመ-አያታቸው ከታቦተ-ጽዮን ጋር ማለት የንጉሥ ሰሎሞንና የንግሥት ሳባ ልጅ ነው የተባለው ቀዳማዊ ምንሊክ ከእስራኤል ታቦተ-ጽዮንን ይዞ ወደ አክሱም ሲመጣ ከሱ ጋር የመጣ እንደሆነ፤ ስለዚህም፤ የኢሮብ ህዝብ ቅድመ አያቶች ከአውሮጳ የመጡ በመሆናቸው ህዝቡ ኢሮብ እንደተባለ የሚያመለክት ነው። ሁለቱም አፈ-ታሪኮች የተገኙት የ፳ኛው ክፍለ ዘመን መጀመርያዎቹ አሥርት ዓመታት ውስጥ ከታተሙት የጣሊያን መፃሕፍቶች እንደሆነም ተመልክቷል።

በዚህ በክፍል ሁለት በአንዳንድ ሌሎች መፃሕፍቶች ውስጥ ስለ ኢሮብ ህዝብና ከኢሮብ ህዝብ ጋር የተዛመደ ትውልድ አላቸው ስለሚባሉ ጎሳዎች የተመዘገበውን እናያለን። ምክኒያቱም የኢሮብ ህዝብ መሠረተ-ትውልድ ለማወቅ የሚደረገው ጥናት ዛሬ ኣዶሓ-ኢሮብ (ሶስት-ኢሮብ) በሚል ስያሜ የሚታወቁ የሱመ ልጆች ነን የሚሉትን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን በሌሎች የትግራይ ወረዳዎችና በኤርትራ ክፍለ ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩ የአፄ ይትባረክ ልጆች ናቸው የሚባሉትን በተለይ ደግሞ የንጉሥ ወረደምሕረት ልጆች ነን የሚሉትን የጨመረ መሆን ስላለበት እነሱ የሚሉትን ወይም ስለነሱ የሚባለውን አብሮ ማየት የግድ ይላል።

እነዚህ ጎሳዎች በተለያዩ የዓጋመና የክልተ-አውላዕሎ ወረዳዎች፣ በቆላ-ሃዘሞና አከለ-መስሓል፣ እንዲሁም በተለያዩ የአከለ-ጉዛይ ወረዳዎች እስከ ሠራየ ድረስ የሚኖሩ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ በሚኖሩባቸው መንደሮችና በተለያዩ ስሞች ይታወቃሉ፤ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ፦ኮርባርያ፣ እገላ-ሐጺን፣ እገላ-ሐምስ፣ እገላ-ደገብስ፣ እገላ-ማይ ሖፃ፣ ሮብራ፣ ደቂ-ዓፅማይ፣ ዓደቀለይቶ፣ ሰብ ደጉዛይ፣ ሰብ ብዘት፣ እገላ-ረቡዕ፣ እገላ-ዕዳጋ ሐሙስ፣ ትምዛእ፣ ወዘተ.

አባ ተስፋይ መድህን ‘ታሪክ ኢሮብ’ (የኢሮብ ታሪክ) በሚል ርእስ በፃፉት መፅሐፍ ውስጥ የንጉሥ ወረደ ምሕረት ልጆች አምስት እንደነበሩ እነሱም ምስማር፣ ዓሚር፣ ሰንበታይ፣ ሱመ እና ሐናከ እንደነበሩ ይገልፃሉ። ቀጥሎም ምስማር በደስአና ወምበርታ አከባቢ የሚኖር ህዝብ ቅድመ-አያት እንደሆነ፣ ዓሚር ‘ዱሉም-ዳ-ላብሃ’ የሚባል በዳሉል አከባቢ የሚኖር ህዝብ አባት እንደሆነ፣ ሰንበታይ የሰባት እገላና የኮርባርያ ህዝብ አባት እንደሆነ፣ ሱመ አሁን ኣዶሓ-ኢሮብ በሚል ስያሜ የሚታወቁትን በሙሉ የወለደ ከመሆኑም በላይ ከወንድሙ ሚስት የወለደውን የትእዛዝ ዘር የሆኑ ህዝቦች በቅናፍና እና እምባ-ካታይ (ሃዘሞ) እንዲሁም በገናሕቲ አከባቢ (ዓጋመ) የሚኖሩ ፯-ገናሕቲ የሚባሉትም የሱ ዘር መሆናቸውን ይገልፃሉ። ቀጥሎም በለምዛ (አከለ-ጉዛይ) የሚኖር ህዝብና በደስአና ወምበርታ (ክልተ-አውላዕሎ) የሚኖር ህዝብ በከፊል የሐናከ ዘር እንደሆኑ ፅፏል። መፅሐፉ ውስጥ ከገፅ 12 እስከ ገፅ 24 የተፃፈውን ተመልከት። አባ ተስፋይ የወረደ-ምሕረት ልጆች ናቸው የተባሉ ጎሳዎች የሚኖሩባቸው አከባቢዎችን በሚመለከት የሚሉት በክፍል አንድ ካየነው ከኮንቲ ሮሲኒ መጽሓፍ ከተወሰደው ጋር የሚመሳሰል ነው። የኢሮብ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጥና የዘር ሐረግን በሚመለከት ያሰፈሩት ግን በክፍል አንድ ኢሮቦች የላስታው የአፄ ይትባረክ ዘር ናቸው ከተባለው በጣም ይለያል።

አባ ተስፋይ የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ከንግሥት ሳባና ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር የተያያዘ መሆኑን ይገልፃሉ። ስለዚህም የኢሮብ ህዝብ ቅድመ አያት እንድርያስ የተባለ ታቦተ-ጽዮን ይዘው ቀዳማዊ ምንሊክን ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ሰዎች አንዱ እንደሆነ እሱም አባት በአባት የያዕቆብ (እሥራኤል) ልጅ የሆነው የጋድ ዘር እንነደሆነ እናቱ ደግሞ ንግሥት ኢሌኒ የእሥራኤሉ የንጉሥ ዳዊት ልጅ እንደሆነች ሰፋ አድርገው ገልጿል (ገፅ 9-15) ይህ አባባል በክፍል አንድ በትግርኛ ቋንቋ ከተፃፈው ጋር ይመሳሰላል፤ በክፍል አንድ በአማርኛ ከተፃፈው ጋር ግን መሠረታዊ ልዩነት እንዳለው ይታያል።

መምህር በርሄ ዝግታ ስለ ኢሮብ ህዝብ የዘር ሓረግና ታሪካዊ አመጣጥ ያሰፈሩት፤ አባ ተስፋይ ካሰፈሩት ጋር ልዩነት የለውም።

ለዮ ራይንሽ (Leo Reinisch) የሚባል አስትርያዊ ፀሓፊ የኢሮብ ሳሆ ቋንቋ በአብሲኒያ (Die Sprache der Irob-Saho in Abessinien) በሚል ርእስ በ1878 ስለ ኢሮብ ቋንቋ በፃፈው መጽሐፉ መግቢያ ውስጥ ኢሮቦች ከዘመናት በፊት ዙላ በተባለው በቀይ ባህር የኢትዮጵያ ጥንታዊ ወደብ በኩል የገቡ የግሪክ ነጋዴዎች ዘር እንደሆኑ፣ ስለዚህም ኢሮብ የሚል ስያሜ እንደተሰጣቸው ይታመናል ይላል። ይህ አባባል የኢሮቦችና የሌሎች የሳሆ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች እምነት እንደሆነም በተጨማሪ ይገልፃል (ገፅ 4)።

ፈተ. ሚካኤል ሓሳማ የተባሉ ኤርትራዊ ደራሲ 'ዛንታ ኤርትራ' በተባለው መጽሐፍ ውስጥ የሰንበታይ ዘር ነው ተብሎ ስለሚታመነው የእገላ-ሐጺን ህዝብ የዘር ሐረግ ስጽፉ የዚሁ ህዝብ ቅድመ አያቶች ከባህር ማዶ በቀይ ባህር የተሻገሩ የዓረቡ የመሓዊ ወይም መዓውያ(1) በሚል ስያሜ የሚታወቅ ጎሳ ዘር ነው ይላሉ። ደራሲው እገላ-ሐጺን መጀመርያ ልሳነ-ምድር (ከፊል-ደሴት) በሆነችው ቡሪ ይኖሩ እንደነበረ በኋላ ከዛ ወደ ዓጋመ ሂደው ይኖሩ የነበሩና እንደገና ወደ ኤርትራ የተመለሱ የዓጽማይ ልጆች መሆናቸውን ያብራራሉ። ይህ ዓጽማይ የተባለው ሰው የሰንበታይ ዘር እንደሆነ ነው የሚታመነው። ደረሲው በመቀጠል ይህ የእገላ-ሓጺን ህዝብ የትውልድ ሐረጉ ከመዓውያ ነው በሚል አፈ-ታሪክ የሚያምን እንደሆነ ለማረጋገጥ በ1970 ዓ.ም. የአከለ-ጉዛይ አስተዳዳሪ በነበርኩበት ወቅት የእገላ-ሐጺን ሽማግሌዎችን ጠይቄ የመዓውያ ዘር መሆናቸውን አረጋግጠውልኛል ይላሉ። ቶርዓና ጸንዓ-ደግለ የተዋጉበት ዘመን ቶርዓ የመሓዊ ዘር የስጋ ዘመዶቻችን ናቸው በማለት ጸንዓ-ደግለ የጠየቁን የገንዘብ እርዳታ አለመስጠታችን አንድ ምልክት ነው እንዳሉትም ደራሲው መዝግቧል። በዚሁ ደራሲ እምነት የሱመና የሓናከ ዘር ናቸው የሚባሉ ህዝቦችም በሙሉ የማዓውያ ዘሮች ናቸው። ለምሳሌ ስለ ሮብራ ህዝብ ሲጽፉ ሮብራ የሐናከ ልጆች መሆናቸውን ይገልጹና መሠረታቸው ከእገላ-ሓጺን አንድ እንደሆነና የመዓውያ ዘር መሆናቸውን ያስቀምጣሉ (ገፅ 63-64)።

በሌላ በኩል ግን እገላ-ሓጺንና ሮብራ የአፄ ይትባረክ ልጅ የሆነው የንጉሥ ወረደ-ምሕረት ልጆች ነን እንደሚሉ ዘግቧል። ደራሲው አፄ ይትባረክ ከ1268 እስከ 1290 በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረ የዛጉ ዘር ነው ካሉ በኋላ እነዚህ ሁለት ጎሳዎች አፄ ይትባረክ ሩፍሉዱምን፣ ዮሐንስንና ወረደ-ምሕረትን ወለደ፤ ዮሐንስ ሱመን፣ ሩፍሉዱም ሰንበታይን ወረደ-ምሕረት ደግሞ ሓናከን ወልዷል፤ ሮብራና ዓጽማይ የሰንበታይ ልጆች ሲሆኑ ዓጽማይ ደግሞ እገላ-ሓጺንን ወለደ ብለው ያምናሉ ይሉና፤ በፅሑፋቸው ውስጥ ወረድ ብለው የእገላ-ሐጺን የዕድሜ ባለፀጋዎችና ሌሎች ከነሱ ጋር የዘር ዝምድና ያላቸው ትልልቅ የመዓውያ ዘሮች እምነት እነዚህ ጎሳዎች የመዓውያ ዘር መሆናቸው ነው ብሎ ይደመድማሉ።

ፈተ. ሚካኤል ሓሳማ በተለያዩ የኤርትራ አውራጃዎች የሚኖር ላምዛ የተባለ ሕዝብም የንጉሥ ወረደ-ምሕረት ዘር መሆኑን ዘግቧል። ህዝቡ መሠረቱ ከዓጋመ መሆኑን እንደሚያምንም ጨምረው አብራርቷል። አመጣጣቸው ከዓጋመ መሆኑን ከማመናቸው በተጨማሪ የንጉሥ ወረደ-ምሕረት ልጆች ነን እስካሉ ድረስ የሓናከ ዘመዶች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሆኖ ይገኛል። ስለዚህም የመዓውያ ዘር ናቸው ቢባል ስሕተት አይሆንም ይላሉ (ገፅ 67)።

በሠራየ የሚኖሩ ትምዛእ የተባሉት በዓጋመ አውራጃ ከሚገኝ ገናሕቲ ከተባለ ቦታ ወደ ኤርትራ የገቡ የሓናከ ልጆች መሆናቸውን፣ ዘራቸው ደግሞ ከመዓውያ እንደሆነ አሥፍረዋል ፈተ. ሚካኤል ሓሳማ (ገፅ 69)።

ጀሜትራ ገብረ ኢየሱስ አባይ የተባሉ ጸሓፊ 'መሠረት ዓሌት ሕዝቢ መረብ ምላሽ' በተባለው መጽሓፍ ውስጥ የኢሮብ ህዝብ ትውልድ ሐረግ ከላሰታ እንደሆነ ጽፏል። እርሳቸው ኢሮቦች የንጉሥ ወረደ-ምሕረት ዘር መሆናቸውን ይመዘግቡና የወረደ-ምሕረት አያት ጀራተ ቀጭን የአባቱ የአፄ ይትባረክ አልጋ የመውረስ ተስፋ እንደሌለው ስለተገነዘበ በ1206 ወደ ትግራይ እንደመጣ እዛም የአከባቢ ተወላጅ ሴት አግብቶ የወረደ-ምሕረትን አባት እንደወለደ ዘግቧል። በመቀጠልም ጅራተ ቀጭን እገላ-ደገብስን፣ እገላ-ሓጺንን፣ እገላ-ሓመስን እና የወረደ-ምሕረትን አባት ወለደ ይሉና ሰንበታይ ሱመና ሓናከ የወረደ-ምሕረት ልጆች እንደሆኑ በመመዝገብ ከሱመ የተወለዱት በዓጋሜ እንደቀሩ የሰንበታይና የሓናከ ልጆች ግን ወደ ሌሎች አከባቢዎች እንደተበተኑ ያስፍራሉ።

ጀሜትራ ገብረ-ኢየሱስ በተለያዩ የትምዛእ (ኤርትራ) ቀበሌዎች የሚኖሩ የወረደ-ምሕረት ዘር መሆናቸውን ይገልፁና ከነሱ ተለይተው የሄዱ ዘመዶቻቸው በዕራዕ (ትግራይ) ይኖራሉ ይላሉ ። ቀጥሎም ላምዛ፣ ዓዲ-ደጊያት አቤነር፣ እገላ-ሐጺን፣ እገላ-ሐመስ፣ ሮብራ፣ ኮርባርያ ወዘተ. የመሳሰሉና ሌሎችም በተለያዩ የኤርትራ ክፍለ ግዛቶች የሚኖሩ የወረደ-ምሕረት ዘሮች እንዳሉ ይገልፃሉ። ጀሜትራ ገብረ-ኢየሱስ በሌላ ገፅ ወረደ-ምሕረት ሱመን፣ ሰንበታይን፣ ሓናከን፣ መስመርንና ሮብአምን

እንደወለደ ይገልጻሉ። በርሳቸው አባባል ሱመ ኢሮብን፣ እገላ-ሓጺንን፣ እገላ-ሐመስን፣ እገላ-ደገብስንና እገላ-ወለስን ይወልዳል ዘሮቹ ደግሞ በኢሮብ (ዓጋመ) እና በተለያዩ የኤርትራ ግዛቶች ይኖራሉ። ፀሓፊዉ የሓናከ ልጆች በዓጋመ ሠፈሩ፤ መስመር ደግሞ የቶርዓ ቅድመ አያት ነው ይላል። ጆሜትራ ገብረኢየሱስ ሱመ ከሚች ወንድሙ ሚስት ወልዶታል የሚባለው የትእዛዝ ዘሮች ናቸው ስለሚባሉትም ሰፋ አድርገው ይፅፋሉ። እነዚህ የትእዛዝ ዘሮች በብዛት በጟ ገናሕቲ እንደሚኖሩም ይገልፃሉ (ገፅ 22-25)። ያም ሆነ ይህ በትግራይ ይኑሩ በኤርትራ በዚሁ ፀሓፊ አባባል የነዚህ ጎሳዎች የትውልድ መሠረት ላስታ ነው ከዛም የአፄ ይትባረክ ልጆች ናቸው።

ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ ‘ኣል ራጋሊ’ (Al Ragali) በተባለው መጽሓፉ ከልዩ ልዩ አፈ‌ታሪክ እንደምናገኘው የኢሮብ ሕዝብ ቅድመ አያቶች ከዓፋር አከባቢ በላዓሲ-ጋደ አድርገው የጉንደጉንደ ገዳም ወዳለበት ደጋማ አከባቢ የመጡ መሆን አለባቸው። እዛ ለተወሰነ ጊዜ ከኖሩ በኋላ ግን ከአከባቢው ሕዝብ ጋር በተፈጠረው ቅራኔ ምክኒያት ወደ ሰሜን አቅጣጫ ለመሄድ የተገደዱ ይመስላል፤ ሽምኤዛና ከደረሱ በኋላ ምሳራሓ የተባለ ቦታ መኖሪያቸው ኣድርገዋል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ባቅራቢያው ከሚገኘው ቢሓት በተባለ መንደር ይኖር ከነበረው መካዳ ወይም ሞካዳ ከተባለው አበሻዊ ጎሳ ጋር የሆነ ቅራኔ ስለተፈጠረ አሁን  ኣዶሓ-ኢሮብ በመባል የሚታወቅ ህዝብ ወደሚኖርበት መሬት ለመሄድ ተገደዱል እዛ ከደረሱ በኋላ ግን አከባቢው ተመችቷቸው ብዙ የቤት እንስሳት አፍርተው ሃበታም ሆኑ ይላል።

ቀጥሎም ደራሲው የሦስቱ ወንድማሞች ዘሮች ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አብረው እዛ አከባቢ እንዳልኖሩ ይገልፃል። በአከባቢው የቀሩ የሱመ ልጆችን መጀመርያ ዶባዓ የተባለ ከኢሮብ በፊት በአከባበው ይኖር የነበረ ጎሳ ያስቸግራቸው እንደነበረ፤ እነሱ (ዶባዓዎች) በተለያዩ ህዝቦች ትብብር ከተመቱ በኋላ ግን አከባቢውን ቀዋሚ አገራቸው አደረጉት ይላል። የሓናከ ነገድ ባልታወቀ ምክኒያት አርቆ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመጓዝ በደስአ ምድር መስፈሩን ይገልጻል።  የሰንበቱ ነገድ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመጓዝ በበለሳ ሰሜንና ደቡብ አከባቢ በሚገኙ እገላ በሚል ስያሜ በሚታወቁ ቀበሌዎች እንደሠፈሩ ይመዘግብና አንዳንዶችን በስም በመጥቀስ የሮዳ ዘሮች በብዘት ወረዳ፣ የለይቶ ዘሮች (ደቂ-ለይቶ) በደብረ-ዳሞ አከባቢ፣ እገላ ሓጺን በአከለጉዛይ መካከል በሚገኝ የታወቀ ወረዳ ውስጥ፣ እና የሮባ ዘሮች በእገላ ሓመስ ወይም ጉራዕ እንደሠፈሩ ገልጿል። በተጨማሪ አንዳንድ የሱመና የሓናከ ዘሮችም የሰንበቱ/ሰንበታይ ዘሮች ወደ ፈለሱባቸው አቅጣጫ ሂደው እንደሠፈሩ ይጠቅሳል። ስለዚህም፤ ዓዲ-ረፋይ በተባለ በአከለጉዛይ በሚገኝ መንደር የሚኖሩት የሓናከ ዘሮች እንደሆኑ፣ እንዲሁም በሠራየ ውስጥ እንዳ-አባሺጉምዶ፣ ቀናፍና፣ ዓዲ-ሰጓጉ፣ ነዊሕ-ዝባን ወዘተ. በተባሉ መንደሮች ውስጥ የሚኖር ትምዛእ የተባሉ ጎሳዎች መረብን ተሻግረው የሠፈሩ የሱመ ዘሮች እንደሆኑ ይገልፃል። ስለዚህ ፣ይላል ኮንቲ ሮሲኒ፣ በደቡባዊ ትግራይ ከሚገኘው ከወንበርታ እስከ ከመረብ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኝ አከባቢ ድረስ በሰፊ መሬት የሠፈረው ህዝብ በመሠረቱ የሳሆ ሕዝብ ነው። ሆኖም በሰሜናዊ ምሥራቅ ዓጋመ ከሚኖሩ ኢሮቦች በስተቀር ሌሎች ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ ማህበራዊና ሥነ-ቍጠባዊ ይዘታቸውን፣ ፖለቲካዊ አስተዳደር ወዘተ በሙሉ አብሮዋቸው በሚኖሩ በአበሾች ቋንቋና ባህል ተከተውታል ይላል።

ኮንቲ ሮሲኒ በሌላ ‘የኢትዮጵያ ታሪክ’ (Storia D’Etiopia) በሚል ርእስ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ፣ አጼ ይኩኖ-አምላክ የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑን ባወጀ ጊዜ (የኢትዮጵያ ንግሥና ከዛጉው ሥርወ-መንግሥት ሰሎሞናዊ ወደ ሚባለው ሥርወ-መንግሥት የተላለፈበት ጊዜ መሆኑ ነው) ማኽል አገር ወስጥ የተሸነፉ ዛጉየዎች ትግላቸውን ለተወሰነ ጊዜ በሰሜን ኢትዮጵያ ከዓፋር መሬት በሰተሰሜን በሚገኝ ተራራማ አከባቢ ቀጥሏል፤ ይህም የኢሮበ አፈ‌ታሪክ ስለ ንጉሥ ይትባረክ በዚሁ አከባቢ ሸፍቶ እንደነበረ የሚተርከውን ይደግፋል ይላል።

በሶስተኛውና የመጨረሻው ክፍል፤ በክፍል አንድና ሁለት የኢሮብ ህዝብ የትውልድ መሠረትና ታሪክን በሚመለከት ስለተጠቀሱ ልዩ ልዩ ተረቶች የግሌን አስተያየት አቀርባለሁ።

## የሥነ ጽሑፍ ምንጮች

1. አባ ተስፋይ መድህን፣ ታሪክ ኢሮብ (ሓፂር መግለፂ)፣ ኅዳር 1993 ዓ ም፤. ዓዲግራት
2. መምህር በርሀ ዝግታ፣ መበቖልን ታሪኽን ህዝቢ ኢሮብ፣ ሕዳር 2000 ዓ/ም
3. ፊተ. ሚካኤል ሓሳማ፣ ዛንታ ኤርትራ (ካልኣይ ሕታም)፣ የካቲት 1986
4. ጆሜትራ ገብረ ኢየሱስ አባይ፣ መሠረት ዓሌት ሕዝቢ መረብ ምላሽ፣ ቤት ማኅተም ኮኮበ ጽባሕ ዘማ.ሐ.ፍ.ሃ. - አሥመራ

5. Conti Rossini, C
 a) Storia D'Etiopia, Dalle Origini All'avvento Della Dinastia Salomonide, Istituto Italiano D'arti Grafiche – Bergamo, 1928.
 b) Al Ragali, Estratti dal Bollettino della "Società Italiana di Esplorazioni Geografiche e Commerciali, Anni 1903-1904

6. Reinisch, Leo, Die Sprache der Irob-Saho in Abessinien, Von Vien 1878 Commission dei Karl Gerold's Sohn Buchhändler Kais Akademie der Wissenschaften.

---

(1) ፊተ. ሚካኤል ሓሳማ ይህ መዓውያ የተባለ ሰው መጀመርያ የመሓመድ ነቢይ ረዳት እንደነበረ፣ በኋላም ደማስቆስን መናገሻውን በማድረግ ነግሦ የነበረ ዓረብ እንደሆነ ሰፋ አድርገው ታሪኩን ጽፏል። በኋላ ግን በኒሃሺም የተባለ ነገድ በኒኡመያ የተባለውን የመዓውያ ነገድ በጦርነት አሸንፈው የራሳቸውን ሰው ስለ አነገሡና በኒኡመያ ዘሮችን እያሳደዱ መፍጀት ስለጀመሩ የመዓውያ ዘሮች ሸሽተው ቀይ ባሕርን በመሻገር ወደ ኤርትራና ትግራይ እንዲሁም ወደ ሌሎች አከባቢዎች ሂደው ሠፍሯል ይላሉ ፊተ. ሚካኤል። እንዲሁም በኤርትራና ትግራይ እስከ ጅቡቲ የሚኖሩ የመዓውያ ኅሳዎች የስም ዝርዝርና የሚኖሩባቸው ቦታዎችን መዝግቧል። ዝርዝሩ ውስጥ ሓዶ (ሓዞ)፣ ቶርዓ፣ሱሩክሶ፣ እገላ-ሓጺን፣ ሮብራ፣ ትምዛእ፣ ላምዛ፣ እንጋንኣ እንዲሁም ሱመና ሓናከ ይገኙበታል።